# ኦሮምኛን በላቲን ፊደል ስለመፃፍ ጉዳይ።

ከሙሉጌታ ውዱ። mooloogeta@hotmail.com
ግንቦት ፲፪ ቀን ፳፻፱ ዓ. ም.

**የፍቅር ቤተሰብና ሰይጣን ያማከረው ቤተሰብ።**

ባልና ሚስት ሴቶችም ወንዶችም ልጆች ይወልዳሉ። ለልጆቻቸውም እርስ በርሳቸው እንዲፈቃቀሩ የፍቅርን ነገር ያስተምሯቸዋል። ወንድምን ለወንድሙ 'ክፉህን የማይሻ መከታህ ነውና ወንድምህን ሁልጊዜ ውደድ' ይሉታል። ለሴቷም እንደዚሁ 'ወንድምሽ ነውና ወንድምሽን ውደጂ ለክፉ ጊዜሽ ይደርስልሻልና' ይሏታል። ወንዶችም እህቶቻቸውን እንዲወዱ ይነግሯቸዋል። እህትና ወንድም፣ ወንድምና ወንድም፣ እህትና እህት እየተዋደዱ፣ እየተሳሰቡና እየተረዳዱ ይኖራሉ። ይነፋፈቁማል።

እንዲህ በሚዋደድ ቤተሰብ ውስጥ ሰይጣን የመግቢያ ቀዳዳ እድሉን ሲያገኝ ይገባና ሄዶ ለአንደኛው ወንድም "ወንድምህ እኮ ወንድምህ አይደለም፤ ጠላትህ እንጂ። እሱ ባይኖር ኖሮ የምትተኛበት ክፍል ያንተ የብቻህ ይሆን ነበር" ይለዋል። ለአንደኛዋ እህት ደግሞ ይሄድና "እህትሽ እኮ ጠላትሽ ናት፤ እሷ ባትኖር ኖሮ እሷ የለበሰችው ልብስ ሁሉ ያንቺ ይሆን ነበር" ይላታል። በዚህ ጊዜ ወንድምና ወንድም፣ እህትና እህት፣ እህትና ወንድም ይናቆራሉ። አንዱ ሌላውን ሊያጠፋ ይነሳሳል። እርስ በራሳቸው ከተጠፋፉ ቤቱን አንዳቸውም ሳያገኙት የሰይጣን ሆኖ ይቀራል።

ከላይ እንደምናየው የተባረከን ቤተሰብ የተረገመ ቤተሰብ ለማድረግ ሰይጣን የሚጠቀምበት መሳሪያ የቤተሰቡን አስተሳሰብ መቀየር ነው።

ኢትዮጵያውያን ለረጅም ዘመናት ከላይ እንዳየነው እንደመጀመሪያው ቤተሰብ በፍቅር ይኖሩ ነበር። ሆኖም ግን በአርዌ ላይ ተሳፍሮ አዳምና ሄዋንን ከመልካሙ ከገነት ኑሮ እንዳሳጣቸው ሁሉ በዘመናችንም ሰይጣን ህወሃት በሚባለው ቡድን ላይ ተሳፍሮ ገብቶ ከላይ እንዳየነው እንደሁለተኛው ቤተሰብ ኢትዮጵያውያንን አቃቅሮ፣ አገርንም ከፋፈሎ እነሆ የሞት አፋፍ ላይ አድርሷታል።

አርዌው አትዮጵያውያንን ከከፋፈለባቸው መንገዶች አንዱ በተለይ የኦሮሞ ተወላጆችን መንፈስ በጥላቻ በማወክ በወንድሞቻቸው ላይ በጥላቻና በልዩነት እንዲቆሙ ማድረግ ሲሆን ከዚህም አንደኛው የግእዝን ፊደል ትተው ከወንድሞቻቸው ተለይተው በላቲን ፊደል እንዲጠቀሙ ማድረጉ ነው። ማንም እንደሚያስታውሰው የዛሬ ሃያ ስድስት አመት በሲ አይ ኤ እና በሞሳድ ታቅፎና ተደግፎ ወደ አዲስ አበባ የገባው ህወሃት በጥላቻ ተሞልቶ ነበር የመጣው። የህወሃት ቋንቋው ጥላቻ፣ እርምጃው ጥላቻ፣ አላማው ጥላቻ፣ ህጉም የጥላቻ ነበር። ያን ጊዜ በጥላቻ ሰብሳቢነት ለጥላቻ የተሰበሰቡት የኦሮሞ ነፃ አውጭ ድርጅት ነን የሚሉት ስብሳቢያቸው የሰበሰባቸው ለጥላቻ ስለሆነ እነሱም የበኩላቸውን ጥላቻ ለሰብሳቢያቸው ለማሳየት ኦሮምኛን በላቲን እንጽፋለን ብለው ተነሱ። ለእርምጃቸው መሠረቱ ጥላቻ እንጂ አቶ ባይሳ ዋቅ - ወያ እንዳሉት በጥናት ላይ የተመሠረተ አልነበረም። ይህንንም በብዙ መንገዶች ማረጋገጥ ይቻላል።

**ነገደ ሳባ ከኩሽ ወይስ ከሴም?**

አቶ ባይሳ ዋቅ - ወያ *"የቁቤ ጉዳይ የማይቸግር ለቸገራቸዉ "አፍቃሪ – ኢትዮጵያውያን""* በሚለው ጽሁፋቸው የሚከተለውን አስተያየት ሰጥተዋል። እውነታቸውን ከሆነና እሳቸው እንዳሉት ሰው መጀመሪያ የራሱን ወይም የወገኑን መፈለግ ካለበት እስኪ ትንሽ ጠለቅ ብለን የሚሉትን እንመርምረው።

አቶ ባይሳ እንዲህ አሉ፦ *"ሊቃውንት ቋንቋቸውን ለማሳደግ በግድ ከሌላ ቦታ መዋስ ካለባቸው በመጀመሪያ ደረጃ "ማማረጡንና ማገላበጡን" መጀመር ያለባቸው ከጎረቤት ነው። በተለይ በቋንቋ ተመሳሳይ የሆነ ወይም በነገድ ቅርበት ያላቸው ሕዝብ ባካባቢው ካሉ የነሱን ፊደላት በመጀመርያ ደረጃ መፈተሹ አግባብ ያለው አሰራር ነው። አማርኛ ተናጋሪ ምሁራንም ለአማርኛ ቋንቋ ማሳደጊያ ፊደላት ለመሸመት ባህር ማዶ መሄድ አልነበረባቸውም። እዚያው በቅርብ ካለው ቤት ዘመድ ከሆነው ከሳባውያን መዋስ ነበረባቸው። ሁለቱም ብሄሮች ከሴም ነገድ ስለሆኑ ከዚህ የተሻለ ዕቃ የትም የቋንቋ ገበያ ላይ ሊያገኙ አይችሉም ነበር።"*

የአቶ ባይሳ የመጀመሪያ ነጥብ "የግዕዝ ፊደል ባለቤት የሳባ ነገድ እንጂ አማራ ወይም ትግሬ አይደለም" ሲሆን ሁለተኛው ነጥባቸው ደግሞ "የሳባ ነገድ የሴም ነገድ ስለሆነና አማራና ትግሬ ደግሞ ከሴም ነገድ ስለሆኑ የግዕዝን ፊደል ከሳባ ነገድ መውሰዳቸው ተገቢ ነው" የሚል ነው። የግዕዝ ፊደል ከሳባ ነገድ ስለመወሰዱ ማስረጃ አላቀረቡም፤ ሆኖም ግን እስኪ ይሁንላቸው ብለን እንውሰደው። አቶ ባይሳ አላወቁትም እንጂ የሳባ ነገድ የሴም ነገድ ሳይሆን የኩሽ ነገድ ነው። ሳባ የሚባል ሌላ የሴም ልጅ አለ ነገር ግን አቶ ባይሳ የሚያወሩት የመን ስለነበረው የሳባ ነገድ ስለሆነ እሱ በብዙ ማስረጃ የኩሽ ልጅ መሆኑ በእኛ ዘንድ ብቻ ሳይሆን የመንን አጠናን በሚሉ ምዕራባውያንም ዘንድ የተረጋገጠ ነው። እስኪ ሁለት ማረጋገጫዎችን እንመልከት፡-

በምእራባውያን ዘንድ የታወቀው አሳሺ እና የአርኪዮሎጂ ምሁር ጀምስ ቴዎዶር ቤንት ኢትዮጵያን እና የመንን እንዲሁም የዐረቦችን አገሮች ሁሉ ካሰሰ በኋላ የመልክአ ምድር ጋዜጣ በተባለው ጽሁፉ የሚከተለውን አስፍሯል።

*"የመን የኩሾች አገር እንደነበረች ፈርሰው የሚገኙት ጥንታዊ ግንቦች (አርኪቴክቸር) በአክሱምና በአዱሊስ ከሚገኙት ጋራ አንድ እጅ እንደሰራቸው ይመሰክራሉ። በየመን የሚገኙት የአለት ጽሁፎችም የሚናገሩት ይህንኑ ነው።... በአንድ ሺህ ስምንት መቶ ዓመተ ዓለም አካባቢ የዮቅታን ነገድ የኩሾች መኖሪያ በሆነው ደቡብ ዐረቢያ ይሰፍሩና በኩሾች ይዋጣሉ። ሰፋሪዎቹ የዮቅታን ነገዶች በየመን የመሬት ባለቤትነት መብት ያላቸው ዝቅተኛ መደብ ሲሆኑ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ስልጣን መሪዎች ሁልጊዝም ኩሾቹ ነበሩ።... የዮቅጣን ነገድ በየመን ሰፍረው በኩሾች ከተዋጡ በኋላ ኩሾቹ ሳባውያን ወደ አቢሲኒያ ተሻግረው በአቢሲኒያ መኖር ጀመሩ[1]።"*

የየመኑ ሳባ ነገድ የኩሽ ነገድ እንደሆነ ሌላ አንድ ማስረጃ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንጥቀስ።

*"የኩሽም ልጆች ሳባ፥ ኤውላጥ፥ ሰብታ፥ ራዕማ፥ ሰቢቃታ ናቸው። የራዕማ ልጆችም ሳባ፥ ድዳን ናቸው[2]።*
በሴፕታልጂቱ መጽሐፍ ቅዱስ ሳባና ድዳን የሚለውን ሳባና ረዳ ይለዋል።

በየመንም ሆነ በአክሱም የሚገኙ የጥንት የአለት ላይ ጽሁፎች በየመንና በኢትየጵያ ከሚኖሩት ነገዶች ውስጥ ሳባና ረዳ ዋናዎቹ እንደሆኑ ይናገራሉ። በኢትዮጵያም ሆነ በየመን ሳባ ሲነሳ ሁልጊዜ ከረዳ ወይም ከድዳን ጋር ስለሆነ ይህ የሳባ ነገድ የኩሽ የመጀመሪያ ልጅ ሳባ ሳይሆን የልጁ የራዕማ ልጅ ሳባ መሆኑን እንለያለን። ስለዚህ ሳባ የኩሽ የልጅ ልጅ ነው።

አቶ ባይሳ ሆይ፡- የግእዝ ፊደል የሳባውያን ነው ካሉ እነሆ ሳባውያን ደግሞ ኩሾች ስለሆኑ ታዲያ ለኦሮሞ የሚቀርበው የኩሽ ፊደል ነው ወይስ የያፌት ልጅ የሮማው ፊደል የላቲን? ሰው የራሱን ትቶ የሰው ድሪቶ ፍለጋ መሄዱ (ያውም በጥላቻ ተገፋፍቶ) አሳፋሪ ምግባር እንጂ አዋቂነት አይደለም። እርስዎም እንግዲህ ይታረሙ።

አቶ ባይሳ አከታትለውም የግእዝን ፊደል አኮስሰው የሚከተለውን ጽፈዋል፡-

*"በኔ ግምት ግን የግዕዝ ፊደል በነጠላው ድምጽ ባለቤትነት እንኳን የኦሮምኛን ቋንቋ ይቅርና የአማርኛን ቋንቋ እንኳ በሚገባ አያገለግልም ባይ ነኝ። እስቲ አቶ አብርሃም የሚቀጥሉትን ለናሙና ያህል ያቀረብኳቸውን የአማርኛ ቃላት በጽሁፍ ሳስቅምጥና ዓረፈተ ነገር ውስጥ ሳይከቷቸው እንድሁ እንዳሉ ምን ለማለት እንደፈለግሁ ይንገሩኝ። ይበላል፡-ኢይበላም፡- የሚበላ ፡ የሚጠጣ፡ ይጠጣል፡- ኢይጠጣም፡-ይከሳል፡- ይፈራል፡- ኢይፈራም፡- ይሰራል፣ ኢይሰራም፡- ይኖራል ፡ እንዳለ ። እነዚህን ከላይ ለምሳሌ ያቀረብኳቸው ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ ካልተካተቱ በስተቀር ለብቻቸው አሻሚ ትርጉም ነው የሚሰጡት። አንባቢ ትርጉሙን እንዲረዳ ከተፈለገ ሙሉ ዓረፍተ ነገሩ መጻፍ አለበት ማለት ነው። በቁቤ ግን ይህ ችግር መቶ በመቶ ተቀርፎአል። ፊደሎቹ ጥንድ ወይም ደባል ቢሆኑም በቁቤ በተጻፈ ዓረፍተ ነገር ውስጥ በምንም ተዓምር ጣምራ ትርጉም ያለው አንድም ቃል ሊገኝ ኢይችልም። ይህ እንግዲህ በቅንነት ላስተዋለው ሰው የኦሮምኛን ቋንቋ በላቲን ፊደል መጻፍ አዎንታዊ ጎኖቹ ብቻ እንዳሉት የሚያሳይ ነው።"*

አቶ ባይሳ ከላይ ያሰፈሩት ቅንነት ብቻ ሳይሆን አስተዋይነትም የጎደለው አስተያየት ነው። ሠርቶ መብላትን እነደማይፈልግ፣ አስቦ መናገርን እንደማይችል፣ አስተውሎ መራመድ እንዳቃተው የሰነፍ ሰው ባህልን የመሰለ አስተያየት ነው የሰጡት። በመጀመሪያ ሁለትና ሶስት "e" ወይም "a" ተመሳሳይ ድግግሞሽ በማደረግ የላቲንን ፊደላት ቁቤ ብሎ መጥራት ለኔ አይኑን ጨፍኖ መብራቱን አጠፋሁባችሁ ከሚል የህፃን አስተሳሰብ ያልተለየ ጅልነት ሆኖ ነው የሚታየኝ። በርበሮች "በርበር ላቲን" እንደሚሉት "ኦሮሞ ላቲን" እንኳን ቢባል እውነቱን

ያነፀባርቃል። ወደ ዋናው ነጥብ እንምጣና ቃላቶቹ አሻሚ እንዳይሆኑ እሳቸው ባቀረቡት አይነት "የላቲን መፍትሄ" እሰኪ ችግራቸውን በግእዝ ፊደል እንፍታላቸው።

ህኑ ፊደሉ ሲደጋገም ይጥበቅ የተደገመው አይነበብ የሚል ይሆንና፡-

ይበላል (እሱ መብል ይወስዳል፣ ይጎርሳል)
ይይበበላል (ምግቡ መብል ነው)
አይበላም (እሱ መብል አይወስድም)
አይይበበላም (ምግቡ መብል አይሆንም)
የሚበላ (ምግብ የሚወስድ፤ የሚጎርስ)
የሚሚበበላ (ምግብ የሚሆን)

ሁሉም የጠቀሷቸው አሻሚ ቃላቶች አቶ ፈይሳ ላቲኑን ተጠቀምንበት ባሉት መንገድ ብንሄድ በግእዝ ፊደላት በዚህ መንገድ በጣም በቀላሉ ይፈታሉ። ትጉህ ለሆኑ አእምሮዎች ደግሞ የግእዝ ፊደል እንዲያውም ከዚህም የተሻለ መፍትሄ አለው። የግእዝ ፊደል የራሳቸው የኦሮሞዎች ስለሆነ ለሚጠብቁ ወይም ለሚላሉ ወይም ደግሞ ኦሮምኛ ብቻ ለሚያወጣቸው ልዩ ድምፆች አዳዲስ ፊደሎችን ከግእዙ ላይ መጨመር ይቻላል። ያን ጊዜ ማንኛውም ኦሮሞ የራሱን ስላዳበረ በሥራው ይኮራል። ነገር ግን ይህ መንገድ ክፋትንና ጥላቻን ያስወገደ ቅንነትንና ትጋትን ይሻል።

አቶ ባይሳ የሳባ ነገድ ኩሽ መሆኑን ስላላወቁ የሳባ ነገድ ዘመዳቸው አልመሰላቸውም ነበርና ታዲያ የሳባ ነገድ ዘመዴ ካልሆነ ዘመዴ ያልሆነውን ለምን የላቲንን ፊደል አልወስድም ነበር ያሉን። የላቲንን ፊደል ለመዋስ ያነሳሳው ጥላቻና የመለያየት ፍላጎት  በመሆኑ 'የሳባ ነገድ ዘመዴ አይደለም' የሚለው አነጋገር የሽፋን አነጋገር እንደሆነ ይሰማኛል። ስለዚህ አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም እንደተባለው መሆኑን ለማሳየትና ፊደሉ የኩሽም ቢሆን ላቲኑ የተሻለ ሆኖ ካገኘነው እንወስደዋለን የሚሉ ስለሚኖሩ፤ የነሱ አስተሳሰብ ሽባ መሆኑን ለማሳየት የሚከተለውን ማነጻጸሪያ አቀርባለሁ።

በህወሃት አስተባባሪነት የኦሮሞ ወኪሎች ነን ባዮች የላቲን ፊደልን ሲዋሱ ከላይ አቶ ፈይሳ እንዳሉት ብዙ የአገላለጽ ችግሮችን ይፈታልናል የሚል ሃሰተኛ ምክንያት በማቅረብ ነበር። አላማቸው "ችግርን ማቃለል" ከሆነ ፊደሉን ከመቀየር ይልቅ ብዙ ከዋክብትን፣ ቅይጦችን፣ ንጥረ ነገሮችንና ብዙ ሌሎች ክስተቶችን የሚገልፀውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ በመዋስ ኦሮምኛን በእንግሊዝኛ መቀየር አይሻልምን? ከጋራ እሴት ይልቅ ነገሮችን ለመግለፅ የተውሶው ይሻላል የሚል አስተሳሰብ ላለው ሰው ፊደሉን ተውሶ ቋንቋውን መተው ፊደሉን ወሰድኩ ያለበትን ምክንያት ውድቅ ያደርገዋል።

**ብልጦቹ የጥላቻ ዘሪዎችና ጅሎቹ የጥላቻ አራማጆች።**

በኢትዮጵያ ውስጥ ጥላቻን የዘሩት የውጭ አገር ሰዎች ጥላቻን መዝራታቸው ለትግሬ ወይም ለኦሮሞ አስበው ሳይሆን ደካማ ናቸው የሚሏቸውን ተጠቅመው ኢትዮጵያውያንን  ለማጨራረስ፣ ኢትዮጵያን ለበመተንና የተፈጥሮ ሃብቷንም እራሳቸው ለመውረስ ስለፈለጉ ነው። እነዚህ የውጭ ሰዎች አፍሪካን ይቅርና ኢትዮጵያን ከየት ወደየት እንዳደረሷት ለማያስተውሉ በትንሹ በሄንሪ ኪሲንጀር ዘመን የነበሩ የአሜሪካ ጽሁፎችን ብቻ ማንበብ ይበቃል[3]። መጨራረሱ ሲያልቅ መገልገያ የሆኑ ትግሬዎችም ሆነ ኦሮሞች በቦታው እንዲኖሩ አይፈቀድላቸውም። ስለዚህ የጥላቻ አኪያሄድ ለትግሬም ሆነ ለኦሮሞ ጅልነት ነው።

ካምፕ ዴቪድ አኮርድ በመባል የሚታወቀው በግብፅ፣ በአይሁዶችና በአሜሪካኖች መካከል ተደረገው ስምምነት ዋነኛ ሰለባ ኢትዮጵያ ናት። ለዚህም ብዙ መረጃዎች አሉ። በ፳፻፬ ዓ. ም. (በፈረንጆች 2011) ግብፅ ውስጥ በነበረው የህዝብ አመፅ ምክንያት አይሁዶችና አሜሪካኖች ተሸብረው ስለነበር ያን ጊዜ በአሜሪካ በጋዜጣ ይወጡ የነበሩ የደህንነትና የስለላ ድረ‌ጅቶች ፅሁፎች    የካምፕ ዴቪድ ስምምነት ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት እንዳለው ያመለክቱ ነበር። ከነዚህም ውስጥ "የግብፅ ቀውስ ስልታዊ መዘዞች" በሚል ርእስ በፈረንጆች 2011 ዓ.ም. በዓለም አቀፍ መረጃ ድርጅት የተፃፈው ዘገባ አንዱ ነው[4]።

አይሁዶችና አሜሪካኖች በግብፅ ቀውስ ቢጨነቁም የማታ ማታ የነሱን ሰው አል ሲሲን በስልጣን ላይ ማስቀመጥ ችለዋል። የግብፁ መሪ አል ሲሲ ከአይሁዶችና ከአሜሪካኖች ጋር ያለውን ውል ስላደሰው አሁንም ኢትዮጵያን የመበታተን ሥራ በሶስቱ ጥምር አሠራር እንደሚካሄድ ኢትዮጵያውያን ማወቅ ይኖርባቸዋል። ከኤርትራ ጀምሮ

እስካሁን ድርስ ኢትዮጵያን በመበታተንና በመከፋፈል ላይ የተመሰረቱ ሃሳቦችና እንቅስቃሴዎች ምንጫቸው እንደገናም የገንዘብና የሃይል ድጋፋቸው የሚመጣው ከነዚህ ጥምር ሃይሎች ነው።

የኤርትራ እንቅስቃሴ የተጀመረውና የተበረታታው በውጭ ሃይሎች ነው። የተጀመረውና ከግብ እንዲደርስ የተደረገው ለውጭ ኃይሎች ጥቅም ነው። ለኤርትራ ሰዎች ለራሳቸው ግን ጉዳት ነው። የኤርትራ ሰዎች ለምን አላወቁም የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም? በርእዮተ ዓለምና በተሳሳተ አስተሳሰብ ልቡናቸውን በመበከል አታለሏቸው። ሲጀመር ሙስሊሞቹን "ከክርስቲያኗ ኢትዮጵያ ብትገነጠሉ በዐረብኛ የምትፅፉበትና የምትናገሩበት የራሳችሁ ሙስሊም አገር ይኖራችኋል" ብለው ነበር ያነሳሷቸው። ሙስሊሞች የሙስሊም አገር ለመመሥረት አመፅ ጀመሩ። በኋላም በነገሩ አሜሪካኖችና አይሁድ ነን የሚሉት በጥልቀት ገቡበት። ለክርስቲያኖችም "የባህር በር ይዛችሁ ብትገነጠሉ ኢትዮጵያን አደህይታችሁ እናንተ ሃብታም መሆን ትችላላችሁ" አሏቸው። ባህሩን አዩና እንገነጠላለን ብለው ከሙስሊሞች ጋር አንድ ሆነው ተነሱ። ኢትዮጵያን በታትኖ ለማጥፋት ካላቸው ፖሊሲ የተነሳ ግብፆች፣ አይሁድ ነን የሚሉትና አሜሪካኖች የኤርትራ ሰዎች ከኢትዮጵያ እነዲገነጠሉ መጠነ ሰፊ የቁሳቁስ፣ የገንዘብ፣ የስለላና የወሬ ስርጭት ድጋፍ አደረጉላቸው። የኤርትራ ተዋጊዎች መሣሪያ የያዙት ለስሙ ነው እንጂ ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ውጊያውን በማህል አገር በኢትዮጵያ የተዋጉላቸው ሲ አይ ኤ እና ሞሳድ የሚባሉት የውጭ የስለላ ድርጅቶች ነበሩ። ኤርትራ እንድትገነጠልም በተባበሩት መንግሥታት መድረክ ያዘጋጁት አሜሪካኖች ነበሩ። የአፍሪካ መሪዎችም በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ኤርትራ እንድትገነጠል ድጋፍ ስጡ እያሉ አሜሪካኖች እያስገደዱን ነው ብለው ምስክርነት መስጠታቸው ይታወሳል። ግብፆች እራሳቸው በቅርቡ በስብሰባ እንዳሉት "ትንሽ ገንዘብ ከሰጠናቸውና የሚሄዱበትን መንገድ ካሳየናቸው የአፍሪካ ስዎችን በራሳቸውና በራሳቸው ጥቅም ላይ እንዲነሱ ማደርግ ቀላል ነው" ያሉት የኤርትራን ስዎች እንዴት እንደተጫወቱባቸው ስለሚያውቁ ነበር።

የትግራይ ስዎችም አኪያሄዳቸው ከኤርትራ ሰዎች ብዙ የተለየ አልነበረም። ህወሃት በአሜሪካኖችና አይሁድ ነን በሚሉት ተኮትኩቶ ያደገው ኤርትራን እንዲያስገነጥል፣ ኢትዮጵያን በዘር ከፋፈሎ እንዲበታትን፣ አማራ በሚል ስም ተዋህዶ ክርስትናን እንዲያጠፋ ነበር። የውጭ የስለላ ድርጅቶች ወኪል የሆኑት የህወሃት መሪዎች ትግሬዎች ስለሆኑ ምንም ይበሉ ምን ብዙ የትግራይ ሰዎች ተከተሏቸው። እንዲያውም ብዙዎቹ በመለስ አምልኮ ተማረኩ። የህወሃት መሪዎች ኢትዮጵያን ያለባህር በር ሲያስቀሩ፣ አማራ ጠላታችን ነውና ቅስሙን ሰብረናል ሲሉ፣ ተዋህዶ ክርስትናን አክሰምናል ሲሉ ቅር አላላቸውም። የህወሃት ተከታይ የሆኑ የትግራይ ሰዎች ትንሽ ማሰብ ነበር የሚያስፈልጋቸው። የህወሃት የጎሳ ፍልስፍና ቢፀና ከህወሃት በኋላ የትግራይ ህዝብ አገር አይኖረውም። ህወሃት ከሁሉም በላይ የትግራይን ህዝብ መቃብር ቆፍሮ ነው የቀበረው። "የትግራይ ህዝብ በእሳት የተፈተነ ወርቅ ነው" በሚል ሽንገላና የተወሰኑ ህንፃዎችን ትግራይ ላይ በመሥራት ህወሃት የትግራይን ህዝብ የዘላለም ህይወት ሃላፊና ጠፊ በሆነ ጊዜያዊ ጥቅም አታልሎ ወደመቃብር አውርዶታል። ሕወሃት የትግራይን ህዝብ ከእግዚአበሔር ጋር አለያይቷል።

አሁንም እንደገና እነዚህ የውጭ ኃይሎች የኦሮሞ ሰዎችን ተጠቅመው ኢትዮጵያን ሊበትኑ መጥተዋል። ለኦሮሞ ሰዎች ያስጨበጧቸው መፈክር "ኦሮሞ ፈርስት" የሚል ነው። የውጭ ሃይሎች የኤርትራ ሰዎችም ይሁን የትግራይ ሰዎች ወይም የኦሮሞ ሰዎች ደህንነት ጉዳያቸው አይደለም። አሁንም እንደገና በአሰብ፣ በሶማሊላንድ፣ በሱዳን፣ በጅቡቲ በኩል ኢትዮጵያን በማነቆ ሊያጠፏት ከበዋታል። የኤርትራ ሰዎችም ይሁን የትግራይ ሰዎች ወይም የኦሮሞ ሰዎች ለነሱ መገልገያ እቃዎች ናቸው። ከተጠቀሙ በኋላ ይወረውሯቸዋል ብቻ ሳይሆን ያጠፏቸዋል። እነሱ የሚፈልጉት በኢትዮጵያ ያሉ የተፈጥሮ ሃብቶችን ነው። እነዚህም ሃብቶች ሳይነኩ ነው የሚፈልጓቸው።

ስለዚህ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በቀጥታም ሆን በተዘዋዋሪ መንገድ የውጭ አገር ከፉዎች ሸር መጠቀሚያ እንዳይሆን እራሱን መጠበቅ አለበት። ሰው ለሰው አገር ሲል የራሱን አገር አያፈርስም። የሌሎች መጠቀሚያ መሆን ደግሞ ወራዳ ምግባር ነው።

---

[1] Geographical Journal, VI, 109-134, with a map facing page 204 (Cited by W.P. Wilson, Director, the Philadelphia Museums, 1911)

[2] ኦሪት ዘፍጥረት ም ፲ ቁ ፲፮

[3] Kissinger Plans Internecine African Bloodbath. EIR Volume 3. 1976

[4] Copley, Gregory. Strategic ramifications of the Egyptian crisis. 2011. http://www.worldtribune.com/worldtribune/WTARC/2011/me_egypt0088_02_01.html